# በመምህር ምህረተአብ ተስፋዬ ላይና በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምዕመን ላይ የሚደረገውን መንግሥት መራሽ ወከባ አጥብቀን እንቃወማለን!

እንደሚታወቀው በቦሌ ክፍለ ከተማ ጥር 27 ቀን 2012ዓም በ22 አካባቢ በውድቅት ለሊት እንደ ወንበዴ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ላይ በመንግሥት ትዕዛዝ በተሰማሩ ታጣቂ ወራሪዎች በመገንባት ላይ ባለችው ቅድስት ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ዘልቆ በመግባት ታቦቷን ካልወሰድን በማለት ሆን ተብሎ ግርግርና ሁከት በመፍጠር ወታደሮች በወሰዱት ሕገወጥና ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ በተነሳው ፀብ አጫሪነት ተኩሰው *ወጣት ሚሊዮን ድንበሩና ወጣት ሚካኤል ፋኖስን* በመግደል ፣ አስራ ሰባት በማቁሰል ፣ ከሰላሳ በላይ የሆኑ ንፁሁን ዜጎችን ካለምንም ጥፋት ወደ እስር በማጋዝ ሕዝበ ክርስቲያኑን ሲያውኩና ደም ሲያፈሱ እንደነጋላቸው ይታወሳል ።

መምህር ምህረተአብ በዚሁ የመንግስት ታጣቂዎች ግፋዊ ግድያ በተፈጸመባቸው ወጣት ሰማዕታት ቀብር ላይ በመገኘት ሰላማዊና መንፈሳዊ የሆነ ሰፋ ያለ ትምህርት መስጠታቸው ይታወቃል ። ቀጥሎም በዚችው ቤተ ክርስቲያንና በጠቅላላው በሐገሪቱ ውስጥ በሚካሄዱ መንግሥት መራሽ ኦርቶዶክሳውያንን ማሳደድ ፣ በርካታ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናትን በማቃጠልና በማፍረስ እንደተሰማሩ ይታወቃል ሆኖም ግን ፣ በተክርስቲያኒቷ እንደነሱ በኃይልና በጉልበት ሳይሆን ለሚፈፅሙት አስነዋሪ ድርጊት በትዕግስትና በፍቅር አፀፋውን በመመለስ ድርጊታቸው ግን አግባብነት የሌለው መሆኑን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኦርቶዶክሳውያን ምዕመን በተገኙበት በቦሌ መድሀኒያለም መንፈሳዊ ትምህርት መስጠታቸውን ተከትሎ መንግሥት የተከታዩ ሕዝብ ብዛት በማየት ታላቅ ፍርሃት ስላደረበት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ወይንም መንግሥትን ከስልጥኑ ለማውረድ የተዘጋጁ ይመስል ውስጡ በፍርሃት ስለራደ በቀጣዩ በቅዱስ እስጢፋኖስ ተመሳሳይ ትምህርት ለመስጠት በሚሄዱበት ወቅት የቤተ ክርስቲያኗን ቅጥር በመዝጋት አውቶማቲክ መሳሪያ የታጠቁ ወታደሮች ወደ ቅጥር ግቢዋ በማሰማራት መምህር ምህረተአብም ሆነ ኦርቶዶክሳውያን ምዕመኑ እንዳይገቡ በማገት ከፍተኛ የሆነ ችግር ሲፈጥሩ ታይቷል ። መንግስት ይህችን ቤተ ክርስቲያንና ምዕመኗን አስፈላጊ ወዳልሆነ አቅጣጫ ለመምራት ፣ ብጥብጥን ለማስነሳት ፣ ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ እንደሆነ ይስተዋላል ። ስለሆነም መላው የኦርቶዶክ እምነት ተከታይና ሐገር ወዳድ ሁሉ ከዚህች ቤተ ክርስቲያን ጎን በመቆም መንግሥት እጁን ከቤተ ክርስቲያኒቷ ላይ እንዲያነሳ በአፅንዖት ይጠይቃል ።

ምንም አንኳ ዛሬ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት 95 በመቶ በላይ የሚሆኑት ከኦርቶዶክስ እምነት ውጪ ያሉ ቢሆኑም ጊዜው የኛ ነው በሚል ስንኩል አስተሳሰብ በመመራት ይህችን

ጥንታዊና ሐገር የገነባች ኦርቶቶክስ ተዋህዶን በማሳደድ ጥፋት እንጂ ልማት ሊገኝ እንደማይችል ሊረዱት ይገባል ። ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ምዕመኗ የማንንም ሃይማኖት ከዚህ ቀደምም ሆነ ዛሬ ፣ ወደፊትም እንደማትጋፋ መንግሥትም ሆነ የመንግሥት የኃይል መሰሪያ የሆኑት ታጣቂዎች ያውቁታል ብለን ከልብ እናምናለን ። ሆኖም ግን ኦርቶዶክስ ተዋህዶን ከኢትዮጵያ ምድር እንድትጠፋ የማድረጉ ሴራዎች ሁሉ የምዕራባውያንና የዐረብ ሐገራት እረጅም እጅ በስልጣን ላይ ካለው መንግሥት ጋር ህብረትን በመፍጠር የሚከናወን እንደሆነ እሙን ነው ። በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና በተከታዮቿ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጫና በመፍጠር ቤተ ዕምነቷንና ምዕመኗን በማሳደድ ፣ በመግደልና ማሰር ፣ የዘወትር አጣዳፊ ተግባራቸው ከሆነ ሰነባብቷል ። ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ግን ፈጣሪዋንና አምላኳን ከጎን በማሰለፍ እንደ መንግሥት ፍላጎትና መንግሥት መራሽ ትንኮሳዎች ፣ በየአካባቢው እንደሚፈፀምባት በደልና ግፍ ኦርቶዶክስም በተመሳሳይ እንድትነሳ የሚገፋፋው እልህ አስጨራሽ መፈታተን በፍፁም ተግባራዊ እንደማይሆንና ትላንትም ፣ ዛሬም ፣ ወደፊትም በሰላማዊ መንገድ አምላኳን መሸሸጊያ ተገን አድርጋ ፣ ምዕመኗን በፅናት ይዛ በድል አድራጊነት ሁሉን እንደምትወጣው ማናቸውም ፀረ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የሆኑ ሁሉ ሊያውቀው ይገባል ።

በማጠቃለልም ዘወትር ቤተክርስቲያኒቷም ሆነች ምዕመኖቿ አበክረው እንደሚሉት *"ኃይል የእግዚአብሄር ነው"* ፣ *"አንመካም በጉልበታችን ፣ እግዚአብሄር ነው ኃይላችን* " እንላለን ። ስለሆነም መንግሥትም ሆነ ሌሎች ፀረ ኦርቶዶክሶች እጃችሁን ከቅድስት ቤተክርስቲያናችን ላይ አንሱ በማለት ደግመን ደጋግመን ልናሳስብ እንወዳለን ።

"ኃይል የእግዚአብሄር ነው" ፣ "አንመካም በጉልበታችን ፣ እግዚአብሄር ነው ኃይላችን"

ታዛቢው

February 11, 2020